[UNofficial compilation] by Abrham Yohanes

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 193294

መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዘሀራ ሰዒድ

ተጠሪ፡- በደቡብ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፉ ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31781 የካቲት 09 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቧ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጂንካ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡-

ተከሰሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 481/4 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 17/2/2011 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ በጂንካ ከተማ በረከት ንዑስ ቀበሌ ልዩ ቦታው ወሎ ሰፈር

ተብሎ በሚጠራው አካባቢ 2ኛ ተከሳሽ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ አመልካች አብራት እንድትኖር በማድረግ ከአመልካች ጋር ሕገወጥ የጦር መሳሪያ በማከማቸት እና ሕገወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ በመፈጸም ለአቶ ታሪኩ ፀጋዬ እና ለወጣት ገዛኸኝ ይደይስ የክላሽ ጦር መሳሪያ ጥይት በቁጥር 200 የአንዱ ዋጋ ብር 85 / ሰማንያ አምስት / በጠቅላላው በብር 17,000 / አስራ ሰባት ሺህ ብር / አመልካች ስትሸጥላቸው ገዥዎች ገዝተው ወደ ኩሬ ቀበሌ እየሄዱ ሳለ በአካባቢው በነበሩ ግለሰቦች ጠቋሚነት ከሁለት መቶ የክላሽ የጦር መሳሪያ ጥይት ጋር በፖሊስ የተያዙ ሲሆን በቀን 18/2/2011 ዓ.ም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የተከሳሽ መኖሪያ ቤት ሲበረበር የንምራ ቁጥሩ 221M208 የሆነ ክላሽ ጦር መሳሪያ፤ 955 / ዘጠኝ መቶ ሀምሳ አምስት ጥይት/፤ 92 የመንቶብ መሣሪያ እና አንድ የክላሽ መሣሪያ ከፎን የተያዘ ሲሆን ከዚህ በፊት በመሰል ተግባር ተሰማርተው የነበሩ በመሆኑም ድርጊቱ የተፈጸመው በአፍቅሮተ ንዋይ እና የዘወትር ሞያ ስራ በማድረግ የተፈጸመ በመሆኑ ተከሳሾች በፈጸሙት ህገወጥ የጦር መሳሪያ መነገድ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዓቃቤሕግን ምስክሮች እንዲሰሙ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የዓቃቤሕግ ምስክሮች ቀርበው አመልካች የጦር መሳሪያ በህገወጥ መንገድ ሸጣላቸው የገዙ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አመልካች በተከሰሰችበት የሕግ አንቀጽ እንድትከላከል የስር 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የተከሰሰችበትን የሕግ አንቀጽ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2 መሠረት በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/3 እንድትከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች መከላከያ ማስረጃ አቅርባ ክሱን ያልተከላከለች በመሆኑ በተከሰሰችበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481/4 መሠረት ጥፋተኛ በማለት በስምንት ዓመት እሥራት እንድትቀጣ በማለት የወሰነ ሲሆን የስር 2ኛ ተከሳሽን ደግሞ ያቀረበችው መከላከያ ማስረጃ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/3 መሠረት ጥፋተኛ በማለት በስድስት ወር እሥራት እንድትቀጣ ወስኖ አፈጻጸሙን በሚመለከት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ገድቦላታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርባለች፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የጥፋተኝነት ውሳኔውን በማጽናት ተጨማሪ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን አሻሽሎ በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንድትቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባለች፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤሕግ አመልካች በአፍቅሮ ንዋይና የዘወትር ሙያ በማድረግ ወንጀሉን መፈጸሜንም ሆነ በክሱ ዝርዝር ላይ የተመለከቱትን የጦር መሳሪያዎች በመኖሪያ ቤቴ ስለ ማከማቸቴ አላስረዳም፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካች የተከሰስኩበትን የሕግ አንቀጽ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2 ድንጋጌ መሠረት በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481/1/ሀ/ ድንጋጌ ስር እንድከላከል ብይን መስጠት ሲገባው በተከሰስኩበት የሕግ አንቀጽ እንድከላከል ብይን መስጠቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካች የጦር መሳሪያ በመኖሪያ ቤቴ አከማችቼ ብገኝ እንኳን ይኸው ተግባር በወንጀል ሕግ ቁጥር 481/1/ሀ ድንጋጌ ሥር ከሚሸፈን በቀር አፍቅሮ ንዋይን ወይም ሙያ አድርጎ መያዝን የሚያሳይ አይደለም፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የክላሽ ጦር መሣሪያ ጥይት በቁጥር 200 የሆነ ሸጣለች ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 481/4 መሠረት ጥፋተኛ የተባለችበትን አግባብነት ከወንጀል ሕግ ቁጥር 481/1/ሀ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ክስ የመሰረተው አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 481/4 ድንጋጌን በመተላለፍ በአፍቅሮ ንዋይ እና የዘወትር የሙያ ሥራዋ በማድረግ በቁጥር 200 ሕገወጥ የክላሽ ጥይት መነገድ ወንጀል ፈጽማለች፤ የምትኖርበት የስር 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሲበረበርም ክላሽ ጦር መሳሪያ፤ 955 ጥይት፤ 92 የመንቶብ መሣሪያ እና አንድ የክላሽ መሣሪያ ከፎን ተገኝቷል በማለት ነው፡፡ በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል በማለት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በእርግጥም አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481/4 በተደነገገው ሁኔታ

ድርጊቱን የፈጸመች መሆን አለመሆኑን በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬነገሮች አመልካች ከተከሰሰችበት የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 481/1/ሀ ማንም ሰው መንግስትን አደጋ ላይ ስለመጣል በተወሰኑት ድንጋጌዎች ከተመለከተው ውጭ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት የጦር መሣሪያዎች፤ ፈንጅዎች ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የሠራ፤ ከውጭ አገር ያስመጣ፤ ወደ ውጭ አገር የላከ፤ ያጓጓዘ፤ የገዛ፤ የተቀበለ፤ ያስቀመጠ፤ ያከማቸ፤ የደበቀ፤ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወሩ ያደረገ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ የተባሉት ዕቃዎች መወረሳቸው ሳይቀር በመቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ሁኔታው ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለችበት የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ አክባጅ ሁኔታን የሚመለከት ሲሆን ጥፋተኛው የተጠቀሱትን ተግባሮች የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም የሙያ ሥራው በማድረግ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን በተከሰሰችበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ሊሉ የቻሉት ያከማቸችውን መሣሪያ ግማሹን ለሌሎች በመሸጥ፤ ግማሹን ደግሞ በቤቷ አከማችታለች በሚል ነው፤ ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ይህ ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481/1/ሀ ላይ እንጂ በአንቀጽ 481/4 ላይ የወንጀል ማቋቋሚያ ሆኖ አልተቀመጠም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ሕገወጥ መሣሪያ ሸጣላቸዋለች የተባሉት ግለሰቦች የዓቃቤሕግ ምስክሮች ሆነው በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች መሣሪያውን የሸጠችላቸው እና እነርሱም የገዙ መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር በእርግጥም አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 418/4 ላይ በተገለጸው ሁኔታ ድርጊቱን የፈጸመችው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም የሙያ ሥራዋ አድርጋ ስለመሆኑ በመግለጽ  ስለመመስከራቸው ወይም ዓቃቤሕግ በሌላ ማስረጃ ይህንኑ ስለማረጋገጡ የስር ፍርድ ቤት  ውሳኔ አያመለክትም፤ አመልካች ከዚህ በፊት በመሰል ድርጊት ጥፋተኛ ተብላ መቀጣትዋም ቅጣትን ከሚያከብድባት በቀር ድርጊቱን በአፍቅሮ ነዋይ ወይም የሙያ ስራዋ አድርጋ ስለመፈጸምዋ ያሳያል ተብሎ ድምዳሜ ሊወሰድብት የሚችል አይደለም፤ ስለሆነም ይህ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 418/4 መሠረት ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ጥፋተኛ ልትባል የሚገባው አድርጎትዋ በሚመጥነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 418/1/ሀ መሠረት ነው በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለችበት የሕግ ድንጋጌ የተቀየረ በመሆኑ ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

[UNofficial compilation] by Abrham Yohanes

አመልካች በዚህ ችሎት ጥፋተኛ የተባለችበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 418/1/ሀ ድንጋጌ በመቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ወይም ሁኔታው ከባድ በሆነ ጊዜ ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 ደረጃ እና እርከን አልወጣለትም፡፡ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመችው ከባድ ሊባል በሚችል ሁኔታ ስላልሆነ በድንጋጌው ከተቀመጠው የቅጣት አማራጭ ውስጥ በመቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት የሚለው ተወስዷል፤ የወንጀል ደረጃውን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች መካከለኛ በማለት የተያዘውን ይህ ችሎትም ተቀብሎታል፤ መካከለኛ ደረጃ ከ 2 ዓመት እስከ 3 ዓመት በመሆኑ የእሥራት ቅጣት መነሻ እርከን 14 ተይዟል፤ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሏት በመሆኑ ቅጣቱ ሲቀል በእርክ 12 ላይ ያርፋል፡፡ በእርከን 12 ያለው ፍቅድ ስልጣን ከሁለት ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከስድስት ወር ነው፡፡ ስለሆነም በዚሁ እርከን ስር አመልካችን ያርማል ሌሎችንም ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበትን አመልካች በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እሥራት እንድትቀጣ፤ የገንዘብ ቅጣቱን በሚመለከት ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90/2 መሠረት በብር 3000 / ሶስት ሺህ / የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጂንካ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 139221/ 2011 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት በቀን 12/09/2011 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀን 16/09/2011 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 14758 በቀን 09/01/2012 ዓ.ም የሰጠው ወሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31781 የካቲት 09 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ጥፋተኛ ልትባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 418/1/ሀ መሠረት ነው በማለት ቅጣቱን አሻሽለን በዚህ ጉዳይ ከታሰረችበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 3000 / ሶስት ሺህ / የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ በማለት ወስነናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- በውሳኔው መሠረት ማስፈጸም ይቻል ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው የስር ፍርድ ቤት እና ማረሚያ ቤት ይድረሰው፡፡
- የሚመለከተው አካል የገንዘብ ቅጣቱን ተከታትሎ ያስፈጽም፡፡

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ